| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "አስተያየት ። " |
| ርእስ ፤ | • "ስላልሾምናቸው ፡ ናቁን ። "<br>• "የዓለም ፡ ነገር ፥ ጥንትም ፡ ተሻሻለ ፡ ሲሉት ፡ የሚባባስ ፡ ነው ። " |
| ደራሲ ፤ | የ"ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፡ አንባብያን ። |
| ዕለት ፤ | ነሐሴ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2011-003 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | (ካንባብያን ፡ የደረሱ ፡ አስተያየቶች ። ) |

# አስተያየት
# Opinion | رأي

## ስላልሾምናቸው ፥ ናቁን!

ሥልጡንሕዝብና ፡ መዜንው ፥ እንኳን ፡ ደኅና ፡ መጣሽ! አዘጋጆቹም ፥ እግዚአብሔር ፡ እንኳን ፡ ድምፃችኹን ፡ ዳግም ፡ ለመስማት ፡ አበቃን!

ለሀገራዊ ፡ ቋንቋችን ፡ ለዐማርኛ ፡ በምታሳዩት ፡ ጥንቃቄ ፡ ለሕዝብ ፡ ያላችኹን ፡ አክብሮትና ፡ ፍቅር ፡ መጠን ፥ እንደ ፡ ወትሮው ፡ ኹሉ ፡ ስላሳየኻና ፡ ስላረጋገጠልኝ ፥ ተደስቼባችኋለኹ ።

የሕዝብ ፡ አገልጋይ ፡ ከቸሎታ ፡ ጋራ ፡ ትሕትናን ፡ መላበስ ፡ ይገባዋል ። እኔ ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ተወልጄ ፡ በማደጌ ፡ እንጂ ፥ ከ 66 ፡ ወዲህ ፡ የተወለዱትስ ፡ ምናልባት ፡ ከሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፥ ከመንግሥት ፡ ሹመኛዎች ፡ ዘንድ ፡ ትሕትናን ፡ አይጠብቁም ። የዛሬዎቹ ፡ ሹመኛዎች ፡ ለሀገራዊ ፡ ቋንቋችን ፡ ተገቢውን ፡ ጥንቃቄ ፡ አያደርጉም ። ከጥቂት ፡ ሀገር ፡ አፍቃሪዎች ፡ በቀር ፥ ከበታች ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ከፍተኛው ፡ ሹመኛ ፥ እንግሊዝኛን ፡ ሳይጨምሩ ፡ አረፍተ ፡ ነገርን ፡ አይጨርሱም ። ከትምህርት ፡ ማነስ ፡ ይኾናል ፡ እንዳንል ፥ አንዳንዶቹ ፡ ባለ"ዲግሪ" ፡ ናቸው ። ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ይኖር ፡ ይኾን ∴ ምናልባት ፥ ለዐማርኛ ፡ ንቀትን ፣ ለእንግሊዝኛ ፡ አክብሮትን ፡ ካላሳዩ ፥ በጧት ፡ እንዳይሻሩ ፡ ሠግተው ፡ ይኾን ∴ ሳይኾን ፡ አይቀርም ፤ ምክንያቱም ፥ ሕዝብ ፡ አልሾማቸውምና ፡ ለምን ፡ ብለው ፡ ሕዝብን ፡ ያክብሩ ∴ እንዲያውም ፡ ዐማርኛን ፡ በሰባበሩት ፡ መጠን ፥ በማዕርግ ፡ ላይ ፡ ማዕርግ ፣ በሹመት ፡ ላይ ፡ ሹመት ፡ እየጨመሩ ፡ እስገነቱ ፡ ጫፍ ፡ መውጣትን ፡ የተማመመኑበት ፡ ይመስላል ።

ሕዝቤ ፡ ሆይ ፡ ራስኽን ፡ አስከብር! ላልሾምካቸውና ፡ ባልሾምካቸው ፡ አትገዛ!

አማረች ፥ ካዲስ ፡ አበባ ።

---

## የዓለም ፡ ነገር ፥ ጥንትም ፡ ተሻሻለ ፡ ሲሉት ፡ የሚባባስ ፡ ነው ።

[...] ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ በምዕራቡ ፡ ዓለም ፡ በደረሰበት ፡ የኢንተርኔት ፡ እገዳ ፡ ብዙ ፡ አልተገረምኩም ። የዓለም ፡ ነገር ፥ ጥንትም ፡ ተሻሻለ ፡ ሲሉት ፡ የሚባባስ ፡ ነው ። የጊዜን ፡ መንገድ ፡ አንድም ፡ በጽድቅ ፣ አንድም ፡ በጽናት ፡ ካልተጓዙት ፡ አይዘለቅምና ፥ በያዛችኹት ፡ ቀጥሉ ፤ ከጐናችኹ ፡ አንለያችኹም ።

ገብረየስ ፥ ከምዕራብ ፡ አውሮፓ ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።